ማነው በለአደራ ?

የሰማዩን ተስፋ - በእምነት ተመልከቶ
በሮም አደባባይ - በተጋድሎ ጸንቶ፤
በአህዛብ መካከል - እንደመሰከረው
እንደ ቅዱስ ጴጥሮስ - አደራ የምሰጠው፤
አበው ያቆዩትን - ዕንቁ ሀብት የሚወርስ
የወረሰውንም - ለትውልድ የሚያደርስ፤
ማንነቱን እንዲያውቅ - በእምነቱ የሚኮራ
ታሪክ ተረካቢ - ማነው ባለአደራ ?
ከቤተ-መቅደሱ - መሠረት ጀምሬ
እንደ ጉልላቱ - ምሥጢሩን ቀምሬ፤
ፅናና መቋሚያው - እንዲሁም ከበሮው
ንዋየ-ቅድሳቱ - ሥዕለ-አድህኖው፤
በእኔ አንድምታ - ሲቀርብ ትርጉማቸው
የፅናው ምሳሌ - በፍሀም የተሞላው፤
ድንግል ለመለኮት - ዙፋን መሆኗን ነው::
ጸናጽል ሲንቧቧ - ዜማውን ሲያዜም
መቋሚያው ሲነሳ - ግራ ቀኝ ሲዘም፤
ከሊቶስጥራ እስከ ቀራንዮ እንደተንገላታ
መስቀል አሸክመው - አይሁድ እንዳዳፉት - በዚያ ጎልጎታ፤
ከግራና ከቀኝ - ከበሮው ሲደለቅ
በጥፊ እንደመቱት - አይሁድ በመሳለቅ፤
ዙሪያው መታሰሩ - ከበሮው በጠፍር
የጌታን ግርፋት - የጅራፉን ሰንበር
የመከራን ጽናት - ለእኛ ሲል መቻሉን - የሚያስረዳ ነበር::
በማለት ላወርሰው - የአባቶቹን እምነት
በመጽሐፍ ከትቤ - እንዲሁም በትውፊት፤
ትውልዱን በሙሉ - ሲቃኘው በትኩረት
ለአደራ የሚበቃ - አዳገተኝ ማግኘት::
የፈጣሪውን ድምጽ - ጥሪውን ሲሰማ
እንደተከተለው - ምንም ሳያቅማማ፤

በሮም ቄሳሮች እጅ - በሰይፍ ተቀልቶ
የሰማዩን ርስት - በእምነት ተመልክቶ፤
እንደመሰከረው - ደሙንም በማፍሰስ
የሚታዘዝልኝ - እንደ ቅዱስ ጳውሎስ፤
ተወግሮ የሚሞት - እንደ እስጢፋኖስ
መናፍቅ ረቺ - እንደ አትናቴዎስ፤
ዲሙንና ጥርሱን - እንዳበረከተው - እንደ ቅዱሱ ሰው - እንደ ፖሊካርፐስ
የዘወትር ዝክሬ - እንደ ዲዮስቆሮስ፤
አጽሙ እነደተዘራው - ሰማዕቱ ጊዮርጊስ
የምይጠፋ ሰምን - ከቅጥሬ የሚወርስ፤
ፍጹም አምላክ ብለው - እንደመሰከሩት
እንደ ቅዱሳኑ - እንደተጋደሉት፤
የእምነት ትሩፋት - የምትኮሩበትን
የያሬድ ዝማሬ - የመላእክትን ልሳን
የዕዝራ መሰንቆ - የዳዊት በገናን፤
የገዳምን ሕይወት - የቅዱሳንን ገድል
እንዴት እንደወጡ - የዓለምን ፃር በደል፤
የሚያስረዳ ታሪክ - የተዋህዶን ምሥጢር
ሊረከብ የሚችል - ይህን ድንቅ ነገር፤
ትውልዱን በሙሉ - ሲቃኘው በትኩረት
ለአደራ የሚበቃ - ተስኖኛል መግኘት::
‹‹ **ታደሸ** ›› ሳይለኝ - አርጅተሻል ብሎ
ሳይቀንስ ሳይጨምር - በክብር ተቀብሎ፤
ለመጪው ትውልዴ - ጠብቆ ሚያወርሰኝ
ማነው ባለአደራ - ጸንቶ ሚረከበኝ ???
ትላለች ተዋህዶ !

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!